CE/211104A
ጥቅምት 26, 2014

# የአቋም መግለጫ - ከተቆርቋሪ ኢትዮጵያውያን

---

ተቆርቋሪ ኢትዮጵያውያን (ተኢ) የተጸንሰውና የተመሠረተው በ"ተቆርቋሪ ኢትዮጵያውያን" ሕብረተሰቡ ገንቢ ክርክር፤ ውይይትና  የተዘክሮ መፍትሄ  ባህል ለማዳበር አስትዋጽኦ ለማምጣት፤

ኢትዮጵያውያን እነደ ማሕረሰብ ባሕሉን፤ ጠበብትነቱን፤ ብሔራዊ የኑሮ ስልቱንና ተፈጥሮ ሀብትና እሴቶቹን ተምርኩዞ ዘላቂ ሰላም፤ ጸጥታና ደሕንነት በመፍጠር ራሱን በራሱ የማሳደግና ታዳጊ ለውጦችን ማምጣት  ያስችለዋል በሚል እምነት፤

ተቆርቋሪ ኢትዮጵያውያን በሕዝቡና በመንግሥት እንዲሁም በዜጎች መካከል ያሉትን ክፍተት፤ በቀና ውይይትና በሚያስተማምን አላፊነት የተገነባ ሁኔታ እንዲዳብር  ከፍተኛ ጥረት ለማድረግ፤

እንደዚሁም በመንግሥት በኩል የዜና ማሰራጬትና በዓለም አቀፍ ሕዝባዊ ግንኙነት ያለውን የሂደት ክፍተት ለማጥበብና በመተባበር ለማጠናከርና ለመገንባት ተቆርቋሪ ኢትዮጵያውያን ሙሉ ድጋፉን ለማበርከት፤

በተጨማሪም ተቆርቋሪ ኢትዮጵያውያን (ተኢ) አገር  ውስጥና ውጪ ካሉት የሲቪክ ድርጅቶች ጋር የኢትዮጵያን  ትክክለኛ ገጽና በጎ አመለካከት በማስፋፋት ፤ በአንጻሩም ሃሰት እና ስም አጥፊ ፕሮፓጋንዳ የሚነዙና አገሪቱን ለማጥፋት የሚሠሩትን ለመቋቋም ነው።